የሰ/መ/ቁ. 129611

ቀን፡- 26/1/2010

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንደሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1. ሳራ ቻላቸው ቀርቧል

2. አለም አምባሉ

3. አባይነህ መለሰ

4. ዘውዱ ምርኳዝ

5. አብይ ደመላሽ

ተጠሪዎች፡- 1. ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነ.ፈ በላይነህ አዳነ

2. ትምህርት ሚኒስቴር ወኪል አበበ ወንድሙ

መዝገቡ የተቀጠረው ምርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ምርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የባህር ዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01268 ታህሳስ 4 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ የአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42384 በ19/07/2008 ዓ.ም በማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የትምህርት ማስረጃ የመስጠት ግዴታን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ሲሆኑ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ እና 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክሱ ይዘት በ1ኛ ተጠሪ የህግ ትምህርት ቤት ከ2000-2006 ዓ.ም ለ6 ዓመት በዲግሪ ደረጃ ትምህርታችንን ስንከታተል ቆይተን ካጠናቀቅን በኋላ ከደንብና መመሪያ ውጭ በግለሰብ መመሪያ የተማርንበትን ማስረጃ የከለከለን በመሆኑ እንዲሰጠን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪም ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ አይገባም፣ አመልካቾች በዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ቢሆንም የመውጫ ፈተና አማካይ ውጤታቸው የትምህርት ሚኒስቴር ካወጣው በታች ስለሆነ ሚኒስቴሩ ካስተላለፈው መመሪያ መሰረት በመከልከሉ ነው ያልተሰጣቸው፡፡ ይህ መመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተተገበረ በመሆኑ ተጠያቂነት የለብንም ትምህርት ሚኒስቴር ጣልቃ ገብቶ ይከራከርልን ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የመጨረሻ ውሳኔ አልሰጠም፣ ለፍ/ቤት የሚቀርብ አይደለም፡ ዩኒቨርሲቲዎች ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ በመሆናቸው መመሪያ መስተላለፋችን

ተገቢ ነው፡ የመውጫ ፈተና የሥርዓት ትምህርቱ አንዱ አካል በመሆኑ ይህን ሳያሟሉ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ስለማይቆጠር አቤቱታቸው ተቀባይነት የለውም ተከሳሽ ራሱን የቻለ ተቋም በመሆኑ ጣልቃ ገብ አይመለከተንም ብለዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ክሱን ሰምቶ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ 2ኛ ተጠሪ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 28/2 /ሀ/ /ለ/ እና አምስት ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ አጣቃላይ የሥርዓተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ፈተና የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለበትና አዋጅ ቁ 650/02 አንቀጽ 97 ደንብና መመሪያ የመውጣት ሥልጣን ያለው በመሆኑ በዚሁ መሠረት የህግ ተማሪዎች ከሚወስዱት የትምህርት ዓይነት በተጨማሪ የመውጫ ፈተና መፈተንና በቂ ውጤት ማምጣት ያለባቸው ስለመሆኑ መመሪያ ማስተላለፉ ተገቢ ነው፡፡ አመልካቾች እየተማርን የወጣ ነው ያሉትም ተቀባይነት የለውም፡፡ በቂ ውጤት ባያመጡም ማስረጃ ማግኘትን አይከለክለንም ያሉትም የመውጫ ፈተና በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የተካተተ በመሆኑ ግዴታቸው ሳይወጡ ማስረጃ መጠየቅ ህጋዊ መሰረት የለውም መመሪያው በረቂቅ ደረጃ ያለና በሚ/ር ዴኤታ የተፈረመ ህጋዊ ነው ያሉትን በተመለከተ በመላው ሀገሪቱ ተግባራዊ የሆነ በመሆኑና ሚ/ር ዴኤታ መፈረሙ ህጋዊ ነው ረቂቅ ሊባል አይችልም በማለት 2ኛ ተጠሪ በሰጠው መመሪያ መሠረት አመልካቾች በቂ የማለፊያ ነጥብ እስካላሟሉ ድረስ 1ኛ ተጠሪ ማስረጃ አልሰጥም ማለቱ ተገቢ ነው በማለት የአመለካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውን ይህን ለማስለወጥ ሲሆን ይዘቱም የትምህርት ሚኒስቴር የፃፈው ደብዳቤ በህግ ያልተደገፈ ሥልጣን ባለው አካል ያልተፃፈ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ፣ ተራ ደብዳቤ እንደመመሪያ በመውሰድ የተሰጠው ውሳኔ የህግ መሠረት የለውም፣ 2ኛ ተጠሪ የተለያየ መልስ መስጠቱ በዝምታ ታልፏል፡፡ ማስረጃ እንዳይሰጥ የሚከላከል ግልጽ ህግ ሳይኖር ትምህርት ማስረጃ መከልከሉ ተገቢ አይደለም፡፡ የመማርና ማስረጃ ማግኘት መብታችንን የጣሰ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው የመውጫ ፈተና ባለማለፋቸው ምክንያት ትምህርት ማስረጃቸው እንዳይሠጣቸው ግልፅ መመሪያ/አዋጅ በሌለበት የተፃፈ ደብዳቤ አለ በማለት ብቻ መከልከሉን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ታዞ 1ኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 19/2/ በተሰጠው የተቋሙን የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ሥርዓተ ትምህርት የመወሰን ሥልጣን መሠረት የመውጫ ፈተና 8 ክሬዲት ሀወር እንዲይዝ ተደርጓል፣ በትምህርት ውስጥም ተካቷል ስለዚህ ይህንን ያላሟላ ተማሪ ዝቅተኛውን መመዘኛ ያላሟላ በመሆኑ ዲግሪ አይሰጠውም፣ አመልካቾች የመውጫ ፈተና ወስደው የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ ውጤት አላመጡም ስለዚህ ሊሠጣቸው አይችልም፣ ሚኒስቴር ዴኤታ ደብዳቤ መፃፉ ሚኒስትሩን ተክቶ የሚሰራ በመሆኑ መመሪያ አድረጎ መውሰዱ ስህተት የለውም፤ በመመሪያው መሠረት ተጠሪ የትምህርት ካሪኩለም ቀርፆ በሴኔት ሌጀስትሌሽን ፀድቆ በ8 ክሬዲት ሀወር እየተሰጠ ነው አመልካቾች ይህንን አላሟሉም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይፀናልን ብሏል፡፡ 2ኛ ተጠሪም በሰጠው መልሱ 2ኛ ተጠሪ

በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 32 መሠረት የትምህርት ስራን በበላይነት እንዲመራ ሲቋቋም ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ እና የትምህርት ጥራት የሚጠበቅበትን ስታንዳርድ በማዘጋጀት በሥራ ላይ እነዲውሉ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የተፃፈው ደብዳቤ ህገ-ወጥ ሊባል አይችልም፡፡ የመውጫ ፈተና የስርዓተ-ትምህርት አካል ሆኖ ስምምነት ላይ ተድሷል በዚሁ በአዋጅ 650/2007 አንቀጽ 49/2/ በዩኒቨርሲቲዎች በህግ በተሰጠው ስልጣን 8 ክሬዲት ሀወር እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ይኸው በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲሰራ በህግ በተሰጠው ስልጣን ሚ/ር ዴኤታው ደብዳቤ ተፃፈ፡፡ ይህም ለተጠሪ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የተፈፀመ ነው፡፡ አመልካቾች የዲግሪ ሠርተፊኬት ያልተሰጣቸው ተጠሪ ከልክሎ ሳይሆን እንደማነኛውም የሕግ ተማሪ የተሰጠውን ፈተና ባለማለፋቸው ነው ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይፅናልኝ ብሏል፡፡ አመልካቾች የመልስ መለስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በሰበር የቀረበው የጹሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብት አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካቾች በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ክፍል ከ2000-2006 ዓ.ም የሚሰጠውን ትምህርት የተከታተሉና የመውጫ ፈተና ወስደው ከ35% በታች ያመጡ መሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካቾች ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ በመሆኑ ከደንብና መመሪያ ውጭ ማስረጃዎችን ተከልክለናል ይሰጠን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ አስተላለፈ የተባለው መመሪያ ቢሆንም በህግ ተቀባይነት ያለው አይደለም የሚል ነው፡፡

በእርግጥ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 28 መሠረት 2ኛ ተጠሪ የትምህርት ሥራን በበላይነት የሚመራና ሀገራዊ የትምህርት ስታንዳርድ፣ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ አጠቃላይ የሥርዓተ ትምህርት ሥልጣንና ፖሊሲ እና ሥርዓተ ትምህርትን መሠረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን አሠራሮችን የማዘጋጀት በየደረጃው የትምህርት ሥራን እንዲሠሩ በህግ ለተቋቋሙ ተቋማት የማስተላለፍና በሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 97 መሰረት ደግሞ 2ኛ ተጠሪን ያቋቋመው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 234/203 አንቀጽ 2/2/ 1ኛ ተጠሪነቱ 2ኛ ተጠሪ መሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ መሠረት 2ኛ ተጠሪ በሚ/ር ዴኤታ አማካኝነት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የመውጫ ፈተና መቁረጫ ነጥብ አስመልክቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲሠራበት የማድረግ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በደብዳቤ እንዲያውቁ እንዲፈፅሙት ተላልፏል፡፡ ዩኒቨርሲቲውም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀጽ 49/2/ በተሠጠው ኃላፊነት 35% በኋላ 8 ክሬዲት ሀወር እንዲኖረው ተደርጎ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት አድርገዋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች በዩኒቨርሲቲው በነበሩበት ጊዜ በህግ ትምህርት ክፍል የተሠጡትን የትምህርት ዓይነቶች መውሰዳቸው ማጠናቀቃቸው እንጂ ይህንን በዩኒቨርሲቲው የሚሰጠውንና የወሰዱትን የመውጫ ፈተና ተገቢውን ውጤት

በማምጣት ማለፋቸው አልተከራከረም፡፡ ይህ ከሆነም ደግሞ በዩኒቨርሲቲም የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቀዋል ሊያስብል የሚያስችል አይደለም፡፡

በሌላ በኩልም ከትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የተላለፈውን ደብዳቤ ከላይ እንደተመለከተው 2ኛ ተጠሪ ባለው ስልጣን መሠረት የተፃፈና ዩኒቨርሲቲውም ተቀብሎ ተግባራዊ ያደረገው በመሆኑ ምንም የሚከላከል ህግ በሌለበት የሚባል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሠጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የጠፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

1/ የባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በ/ቁ 01268 ታህሳስ 04 ቀን 2008 እና የአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42384 በቀን 19/07/2008 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ. 40215

ታህሣሥ 14 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች፦** ፀጋዬ ወርቅአየሁ

ኃ/ማርያም ሞገሥ

አብዬ ካሣሁን

ተስፋዬ ዓለማየሁ

በሪሁን አዱኛ

**አመልካች** ...... በረከት እንደሻው ህንፃ ሥራ ተቋራጭ ኃላ/የተ/የግ/ማኀ

**ተጠሪ** ......... አሁን ደሳለኝ

ይበልጣል ቢሻው

ጌታቸው ተረፈ

ማስተዋል ብርሃኑ

ሀይማኖት ደምሴ

ሀይማኖት ደጀኔ

ሶስና ብርሃኑ

ትግስት አየነው

አንጓች ሲሳይ

ትግስት አየነው

ትግስት ጌትነት

ሁሉአገርሽ ታከለ

በላይነሽ ስንቴ

ይርበብ ውበቴ

መሠረት ሙሉየ

ፈንታየ ማሩ

ስንቴ ፍቃዱ

መሠረት ባዜ

ሰላም አድማሱ

ሁሉአገርሽ ቸኮል

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፤ በዚሁ መሠረት መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

## ፍርድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የተነሳው በባህር-ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች መጋቢት 04 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በተለያየ ሙያ እና የደመወዝ መጠን ተቀጥረን በለሳኝነት፣ በአናጺነት፣ በጠራቢነት ሙያ ተቀጥረን በመሥራት ላይ እንገኛለን። ይሁንና የአመልካች ድርጅት ለህዝብ በዓላት እና ለሳምንት የዕረፍት ቀናት ክፍያ ፈጽሞልን

የማያውቅ በመሆኑ ይህ ክስ ከመቅረቡ ከስድስት ወራት በፊት ያለውን የዕረፍት ቀናት እና የበዓል ቀናት ክፍያ ታስቦ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ አቤቱታቸው የወል የሥራ ክርክር በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም፤ የሣምንት እና የበዓላት ቀን ክፍያ ሊከፈል የሚገባውም የወር ተከፋይ ለሆነ እንጂ በየአሥራ አምስት ቀኑ ክፍያ ለሚፈጸምለት ሠራተኛ አይደለም፡፡ ስለሆነም ለበዓላት እና ለሣምንት ዕረፍት ክፍያ የምንፈጽምበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የሳምንት ዕረፍት ቀናት እና የበዓላት ቀናት ክፍያ ሊፈጸምባቸው የሚገቡ ስለመሆኑ በህገ-መንግሥቱም ሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ህጉ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት በክስ የተጠየቀውን ክፍያ ሊፈጽም ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልች በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ለምዕራብ ጎጃም መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታውን ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አቤቱታው ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አመልካች ተጠሪዎች የወር ተከፋይ ሳይሆኑ ለሣምንት የዕረፍት ቀናት እና ለህዝብ የበዓል ቀናት ክፍያ እንድንፈጽምላቸው መወሰኑ ስህተት ስለሆነ ሥር ፍርዱ ይሻርልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው የሥር ፍርዱ መሠረታዊ የህግ ሥህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ቅሬታው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክርክሩም በዚሁ ተጠናቋል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በጉዳዩ ላይ ውሳ የሚሻው ነጥብ ለሣምንት እነወ ለቀን ተከፋይ ሠራተኞች የሣምንት የዕረፍት ቀናት ክፍያ እና የበዓል ቀናት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው በመሆኑ እንደሚከተለው በየተራ እንመለከታቸዋልን፡፡

በቅድሚያ ተጠሪዎች የሣምንት የዕረፍት ቀናት ክፍያ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 (2) ላይ እንደተገለጸው ሠራተኞች ከክፍያ ጋር የዕረፍት ቀን እንደሚያስፈልጋቸው ተገልጿል፡፡ ይህን ዕውን ለማድረግም ማንኛውም ሠራተኛ በአሠሪና ሠራተኛ ህጉ በአንቀጽ 61 ላይ ከቀን 8 ሰዓት፣ በሣምንት ከ48 ሰዓት ሣይበልጥ መሥራት እንዳለበት ሲደነግግ በአንቀጽ 69 ላይ ማንኛውም ሠራተኛ በሰባት ቀናት ውስጥ ያልተቆራረጠ ከ24 ሰዓት የማያንስ ዕረፍት ጊዜ እንደሚያስፈልገው ተገልጿል፡፡ በልዩ ሁኔታ ካልተወሰነ በቀር የሣምንቱ የመጨረሻው ዕሁድ ቀን የሣምንቱ የዕረፍት ቀን እንደሚሆን አንቀጽ 69 (2) ላይ ተገልጿል፡፡ በህገ-መንግሥቱም ሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ህጉ ላይ እንዲህ ያለ ድንጋጌ የተቀመጠው ሠራተኛው ህይወቱን ተገቢ በሆነ መንገድ እንዲመራ (decent life እንዲመራ ለማድረግ) ለማስቻል ነው፡፡ ለሠራተኛው ጥበቃ በማድረግ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ ስንነሳ ሠራተኛው የሣምንት የዕረፍት ቀናትን ያለክፍያ እንዲያሳልፍ ማድረግ ህጉ ሠራተኞች ህይወታቸውን ተገቢ በሆነ መንገድ እንዲመሩ ለማስቻል ህጉ የቆመለትን

መሠረታዊ ዓላማ የሚያስት ይሆናል፡፡ ጥበቃው ተደርጓል ማለት የሚቻለው የሣምንት የዕረፍት ቀኑ ከክፍያ ጋር ሲሆን ብቻ ነው፡፡

ስለሆነም የሣምንት የዕረፍት ቀናት ከክፍያ ጋር መሆን እንዳለበት መታሰብ አለበት፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በሶሺዮ ኢኮኖሚክ ኮቬናንት በአንቀጽ 7 ላይ የዕረፍት ቀናት ከክፍያ ጋር መሆን እንዳለባቸው የተደነገገ እና ኢትዮጵያም የዚህ ኮቬናንት ፈራሚ አገር በመሆኗ በስምምነቱ ተገዳጅ ነች፡፡ ስለሆነም የሣምንት ቀናት ከክፍያ ጋር የመሆኑ ነገር አከራካሪ ባለመሆኑ አመልካቾች ለሣምንት የዕረፍት ቀናት ያልተከፈላቸውን ደመወዝ ተጠሪ ሊከፍላቸው የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ሥህተት ፈጽሟል ማለት አይቻልም፡፡

ወደበዓል ቀናት ክፍያዎች ስናልፍ በአዋጁ አንቀጽ 74 የወር ደመወዝ ተከፋይ የሆነ ሰው በበዓል ቀን ባለመሥራቱ የሚያገኘው ደመወዝ የማይቀነስበት መሆኑ ሲገልጽ ከዚህ ውጪ (ከወር ተከፋዮች ውጪ) ክፍያ የሚፈጸምላቸው ሠራተኞች በተመለከተ ግን ክፍያው በህብረት ስምምነት እንደሚወሰን ይገልጻል፡፡ ምን ማለት ነው? በህብረት ስምምነት ካልተወሰነ በቀር አይከፈላቸውም ማለት ነው ወይስ ሌላ ትርጉም አለው የሚለውን በጥሞና ማየት ይጠይቃል፡፡ ከህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች ስንነሳ በአንቀጽ 42 (2) ላይ "... **ከክፍያ ጋር የሚሰጡ** የዕረፍት ቀኖች፣ **ደመመዝ የሚከፈልባቸው** የህዝብ በዓላት...." የሚሉት ቃሎች የሚሳዩት የዕረፍት ቀኖችም ሆነ የበዓል ቀኖች **ክፍያ/ደመወዝ** የሚፈጸምባቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህን መሠረታዊ ነገር በመያዝም የአ.ሠ.ህ.አ.ቁ. 377/96 አንቀጽ 73 የህዝብ በዓላት ቀኖች ክፍያ የሚፈጸምባቸው መሆኑን ያጸናል፡፡ በአንቀጽ 74 ደግሞ የወር ተከፋይ የሆኑ ሠራተኞች የቀን ደመወዛቸው ምን ያህል እንደሚሆን የሚታወቅ/የሚያከራክር ባለመሆኑ ሠራተኛው በዚህ የህዝብ በዓል ቀን ባይሠራም ደመወዙ (በቀን ሊያገኝ የሚችለው) አይቀነስበትም በማለት ይደነግጋል፡፡ በአንቀጽ 74 (2) ላይ ከወር ተከፋዮች ውጪ የቀን ተከፋዮችን በተመለከተ ግን የቀን ደመወዛቸው እንደሥራው ጠባይ በሚሰሩበት የሥራ ሰዓት የሚወሰን በመሆኑ መጠኑ ሊለያይ የሚችል በመሆኑ ሠራተኞች በበዓል ቀን ምን ያህል ክፍያ ሊፈጸምላቸው እንደሚገባ ለማወቅ ያስቸግራል፡፡ በዚህ የተነሳም አሠሪውና ሠራተኛው በህብረት ስምምነት **የክፍያውን መጠን** እንዲወስኑ ክፍት አድርጎታል፡፡ ይህ ማለት ለሥራ ውል እና ለህብረት ስምምነት የተተወው የክፍያውን መጠን ብቻ ነው፡፡ እንጂ በህብረት ስምምነት ወይም በሥራ ውል ካልተወሰነ በቀር ከወር ተከፋዮች ውጪ ያሉ ሠራተኞች የበዓል ቀን ክፍያ አይፈጸምላቸውም ማለት አይደለም፡፡ በድንጋጌው ላይ በህብረት ስምምነት ይወሰናል ከሚለው ሃረግ ተነስቶ ሠራተኛው በሥራ ውል ወይም በኅብረት ስምምነት እንዲወሰን ለማድረግ ከአሠሪው ጋር እንዲደራደርበት የሚደረገው ከመነሻው የሌለውን፣ ያልተጠበቀለትን የክፍያ መብት እንዲያገኝ ለማስቻል ነው ብሎ ከተፃፈው ነገር ተነስቶ ያልተፃፈውን በማንበብ የሚገኘውን የአተረጓጎም ስልት (acontrario reading) በመቀበል ልንገኝ የምንችለውን ትርጉም በከፍተኛ ጥንቃቄ ልናየው የሚገባ ነው፡፡ አመክኗዊ (logical) የሚመስሉ ነገሮች ሁሉ ትክክለኛ መደምደሚያ ላይ ያደርሳሉ ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ በዚህ የተነሳ እንደህ ያለውን አተረጓጎም በከፍተኛ ጥንቃቄ ልንፈጽመው የሚገባ እንጂ እንደዘወትር የአተረጓጎም ስልት የምንጠቀምበት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ያልተፈለገ/ምክንያታዊ የሆነ ውጤት ላይ ሊያደርሱን ስለሚችሉ ማለት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንዲህ ያለውን አተረጓጎም መቀበል

በመጀመሪያ ደረጃ የክፍያውን አፈጻፀም መሠረት በማድረግ ብቻ የወር ተከፋይ በሆኑን እና የወር ተከፋይ ባልሆኑት መካከል ምክንያታዊ ያልሆነ ልዩነት በመፍጠር የወር ተከፋይ ያልሆኑት ለበዓል ቀን ክፍያ እንደማይፈጸምላቸው በማድረግ ከወር ተከፋዮች ጋር በዕኩልነት የመታየት ህገ-መንግሥታዊ መብታቸውን የሚጥስ ይሆናል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በሣምንት የዕረፍት ቀናት እና በህዝብ የበዓል ቀናት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው በህጉ ላይ የተቀመጠበት ዋና ምክንያት ሠራተኛው ህይወቱን ተገቢ በሆነው መንገድ (decent life) እንዲመራ ለማስቻል ነው፡፡ መሠረታዊ ዓላማው ይህ ከሆነ ምክንያቱ ለወር ተከፋዩ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለቀን ተከፋዩም ተፈፃሚ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፡፡ በሶሺዮ ኢኮኖሚክ ኮቬናንት በአንቀጽ 7 ላይ ሠራተኞች በበዓል ቀናትን ክፍያ የማግኘት መብት እንዳላቸው የተደነገገ እና ኢትዮጵያም የዚህ ኮቬናንት ፈራሚ አገር በመሆኗ በስምምነቱ ተገዳጅ ነች፡፡ ስለሆነም ህገ-መንግሥቱን፣ የአሠሪና ሠራተኛ ህጉን እና ኮቬናንቱን በማገናዘብ አስተሳስረን ስንመለከተው ህግ አውጪው ከዚህ ስሜት በመራቅ የወር ተከፋይ ያልሆኑ ሠራተኞች በስራ ውላቸው ወይም በህብረት ስምምነት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የሚፈቅድ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ለበዓል ቀን ክፍያ አይፈጸምላቸውም ብሎ አቀዋም እንደወሰደ ማሰብ አይቻልም፡፡ እንዲያውም ድንጋጌው ብዙ ጊዜ ከሠራተኞቻቸው ጋር በድርድር የኅብረት ስምምነት ለመፈጸም የማይፈልጉ አሠሪዎችን የህብረት ስምምነት እንዲኖራቸው የሚያተጋ መሣሪያ ተድርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ከዚህ ያለፈ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡ ስለሆነም የወር ተከፋይ ያልሆኑ ሠራተኞች ከአሠሪያቸው ጋር በሥራ ውል ወይም በህብረት ስምምነት የሚወስኑት ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች የክፍያውን መጠን ብቻ ነው፡፡ በህብረት ስምምነት ወይም በሥራ ውል የተወሰነ የክፍያ መጠን ከሌለ ግን ማንኛውንም ሠራተኛ በቀን ስምንት ሰዓት እንደሚሰራ ታስቦ በመርህ ደረጃ የተጠበቀለትን ክፍያ የማግኘት መብት ተግባራዊ ሊሆንለት ይገባል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለበዓል ቀናት ክፍያ ይገባቸዋል በማለት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

አመልካቾች ለሳምንት የዕረፍት እና ለበዓል ቀናትን ክፍያ ሊፈጸምላው ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ ህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

ኪሣራና ወጪ ይቻቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

የባህር-ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔው የጸና መሆኑን አውቆ በጸናው ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍለት፡፡ ይጻፍ፡፡

የተሰጠ ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡